መልእክት ስምንት

## ወንዱ-ልጅ፣ በሰማይ ያለው ጦርነት
## እና ድል የሚነሡት ቅዱሳን

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ራእ. 12፥5፣ 7-11

**I. "አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ"—ራእ. 12፥5፡-**

ሀ. እዚህ *ወለደች* የሚለው በሐዋርያት ሥራ 13፥33-34 እንዳለው ትንሣኤን ያመለክታል፡-

1. ወንዱ-ልጅ ሞተው ከነበሩትና ከሞት ከተነሡት ድል የሚነሡ ቅዱሳን የተዋቀረ ነው።
2. ይህ በራእይ 12፥11 *እስከ ሞት ድረስ* በሚሉት ቃላት ተረጋግጧል።

ለ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ ሴት ደካማ የሆኑትን፣ ወንድ ጠንካራ የሆኑት ያመለክታል—1 ጴጥ. 3፥7፡-

1. በራእይ 12 ያለው ወንዱ-ልጅ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጠንካራ ክፍል ያመለክታል።
2. ወንዱ-ልጅ አሕዛብን በብረት በትር የሚገዛ መሆኑ፣ በ2፥26-27 እንደተጠቀሰው ወንዱ-ልጅ ድል ነሺዎችን እንደሚያካትት ያመለክታል።

ሐ. መወሰድ (አ.መ.ት.) ማለት መነጠቅ ነው፡-

1. የወንዱ-ልጅ መነጠቅ በ 1ኛ ተሰሎንቄ 4፥17 ከተጠቀሰው ከብዙሃኑ አማኞች መነጠቅ ይለያል።
2. በ 1ኛ ተሰሎንቄ 4፥17፣ ሰባተኛው መለከት የሆነው (ራእ. 11፡15) ኋለኛው መለከት ሲነፋ (1 ቆሮ. 15፡52፤ 1 ተሰ. 4፡16) ብዙሃኑ አማኞች ወደ አየር ይነጠቃሉ።
3. በራእይ 12፥5፣ ከስድስተኛው ማኅተም ጀምሮ ከአምስተኛው መለከት በፊት (9፥1) የሦስት ዓመት ተኩል ከሆነው ከታላቁ መከራ (አርባ ሁለት ወራት፣ 12፥14፤ 13፥5፣ 11፥2) ከአንድ ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ቀናት በፊት ወንዱ-ልጅ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ይነጠቃል።

**II. "በሰማይም ሰልፍ (ጦርነት) ሆነ"—12፥5፡-**

ሀ. ወንዱ-ልጅ ወደ ሰማይ ከተነጠቀ በኋላ፣ ወዲያውኑ ሚካኤልና መላእክቱ ሰይጣንን መዋጋት ጀመሩ፡-

1. የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠንካራ ክፍል የሆነው ወንዱ-ልጅ፣ የእግዚአብሔርን ጠላት፣ ሰይጣንን በመዋጋት ሁልጊዜ እንደሚሳተፍ ያመለክታል።
2. በምድር ላይ ሰይጣንን ያለማቋረጥ ሲዋጉት ነበር።
3. ሰይጣንን ከሰማይ ለመጣል ውጊያ ይከፈት ዘንድ እስኪደርሱ ሰማይ እየጠበቃቸው ነው።
4. መጽሐፍ ቅዱስ የሁለት መላእክትን ስሞች—ሚካኤል እና ገብርኤል—ይገልጣል።
5. ገብርኤል ለእግዚአብሔር ሕዝብ ዜናዎችን የሚያመጣ ዘጋቢ ነው (ዳን. 8፥16፤ 9፥21-22፤ ሉቃ. 1፥19፣ 26)፤ ሚካኤል ደግሞ ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ የሚጋደል ተዋጊ ነው (ዳን. 10፥13፣ 21፤ 11፥1፤ 12፥1፤ ይሁዳ 9)።

ለ. "ዘንዶውና መላእክቱም መልሰው ተዋጓቸው" (ራእ. 12፥7 አ.መ.ት.)፤ እነዚህ መላእክት በእግዚአብሔር ላይ ለማመጽ ሰይጣንን የተከተሉት የወደቁ መላእክት መሆን አለባቸው (ማቴ. 25፥41)።

ሐ. የእግዚአብሔር ጠላት የሆነው ሰይጣን በጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተፈርዶበታል—ዮሐ. 12፥31፤ 16፥11፡-

1. ከዚያ በኋላ፣ ያን ፍርድ ለማከናወን፣ ያን የፍርድ ወሳኔ ለማስፈጸም ድል የሚነሡ አማኞች ያስፈልጋሉ።
2. ድል በሚነሡ አማኞች በሰይጣን ላይ የሚከፍቱት ውጊያ በእርግጥም በእርሱ ላይ የጌታን ፍርድ ማስፈጸም ነው።
3. በስተመጨረሻ፣ በመዋጋታቸው በኩል ሰይጣን ከሰማይ ይጣላል—ራእ. 12፥7-9።

**III. "አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ፥ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና። እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ [ዲያብሎስን] ድል ነሡት፥ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም"—ቁ. 10-11፡-**

ሀ. ከበጉ ደም የተነሣ ድል ነሡት፡-

1. ሰይጣን ይከሰን ይሆናል፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ እንደሚያነጻን መመለስ እንችላለን—1 ዮሐ. 1፥7።

2. ከተናዘዝንና ደሙን ከተገበርን በኋላ እውነተኛ የሚመስል የትኛውም የማያቆም ኩነኔ የእግዚአብሔር አብርሆት መስጠት ሳይሆን የሰይጣን ክስ ነው—ቁ. 9።
3. መቃወም ያለብን ምክንያት አልባ ክሶችን ብቻ ሳይሆን፣ ምክንያት ያላቸውን ክሶችንም ሁሉ መቃወም አለብን።
4. ኃጢአት በምናደርግ ጊዜ፣ እግዚአብሔርን አናከብረውም፣ ነገር ግን ክቡር ደሙን በማንታመንበት ጊዜ፣ ይበልጥ ክብሩን ዝቅ እናደርጋለን—ማቴ. 26፥28፤ ተዛ. ዕብ. 10፥29።
5. ምንም እንኳ እኛ ፍጹም ባንሆንም፣ በክቡር ደሙ እንደተሸፈንን ለዲያብሎስ በመንገር ሁልጊዜ ደሙን መተግበር አለብን—1 ጴጥ. 1፥18-19፤ ሐዋ. 20፥28።

ለ. ከምስክራቸው ቃል የተነሣ ድል ነሡት፦

1. “ምስክር” ማለት በክርስቶስ ምን እንዳለ ለሌሎች መንገር ነው፤ የምስክር ቃል ደግሞ በግልጽ መታወጅ ያለበት ነገር ነው።
2. ድል ነሺዎቹ ዲያብሎስ በጌታ እንደተፈረደበት በመመስከር በተደጋጋሚ የክርስቶስን ድል ማወጅ አለባቸው—1 ዮሐ. 3፥8፤ ዕብ. 2፥14።
3. ሰይጣን በምክንያት ልናሳምነው ስንሞክር አይፈራም፤ የክርስቶስን ድል ሃቆች ስናውጅ ግን ይፈራል—ተዛ. 2 ዜና 20፥20-22፦
   ሀ. የኢየሱስ ስም ከስሞች ሁሉ በላይ መሆኑ ለሰዎች ብቻ ሳይሆን ለሰይጣንም ጭምር በእምነት ልናውጀው የሚገባ መንፈሳዊ ሃቅ ነው—ፊልጵ. 2፥9-11፤ 1 ቆሮ. 12፥3።
   ለ. ለሰይጣንና ለአጋንንቱ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ፣ ጌታ አሸናፊ እንደሆነ እና ሰይጣን ከእግሩ በታች እንደተቀጠቀጠ ማወጅ አለብን—ዘፍ. 3፥15፤ ዮሐ. 14፥30፤ ሮሜ 16፥20።

ሐ. ነፍሳቸውን እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም፦

1. ከአዳም ውድቀት የተነሣ፣ ሰይጣን ራሱን ከሰው የነፍስ-ሕይወት—ከሰው እኔነት—ጋር አጋጠመ፤ እርሱን ድል ለመንሣት የነፍስ ሕይወታችንን መውደድ የለብንም፤ ይልቁንም፣ ልንጠላውና ልንክደው ይገባል—ማቴ. 16፥23-24፤ ሉቃ. 14፥26፤ 9፥23፦
   ሀ. ሰይጣን በራሳችን ጥንካሬ ነገሮችን እንድናደርግ እና በነፍሳችን፣ በተፈጥሮአዊ ችሎታችን ኃይል እንድንንቀሳቀስ ይፈልጋል።
   ለ. ተፈጥሮአዊ ችሎታ በመጀመሪያ የነበረንና በመስቀሉ አሠራር ታድቦ የማያውቅ ችሎታ ነው።
   ሐ. የቤተ ክርስቲያን ውድቀት ሰው የራሱን ተፈጥሮአዊ ችሎታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከማምጣቱ የተነሣ ነው።
   መ. የመስቀሉ ዓላማ በጴጥሮስ እና በሙሴ ታሪክ እንደታየው በራሳችን ለመንቀሳቀስ እንዳንደፍር ተፈጥሮአዊ ጥንካሬያችንንና ችሎታችንን ለማደብ ነው—ሐዋ. 7፥23-30፤ ሉቃ. 22፥32-34፤ 1 ጴጥ. 5፥5-6።
   ሠ. በየትኛውም መንገድ በራሳችን አንኖርም የሚል አመለካከት ሊኖረን ይገባል፤ ለራሳችን ችሎታ ዋጋ አንሰጥም ወይንም በራሳችን ምንም መታመን አይኖረንም—1 ቆሮ. 2፥2-4፤ ፊልጵ. 3፥3፤ ተዛ. ኢሳ. 11፥2።
2. ክርስቶስ እንደ ሰማያዊው የወይን ጠጅ እንዲሞላንና ለእግዚአብሔር የወይን ጠጅ እንዲያደርገን በመፍቀድ ራሳቸውን-የሚሠዉ ሰዎች፣ የመጠጥ ቁርባን መሆን አለብን—ፊልጵ. 2፥17፤ 2 ጢሞ. 4፥6፤ መሳ. 9፥13፦
   ሀ. የመጠጡ ቁርባን፣ ለእግዚአብሔር እርካታ እንደ እውነተኛው የወይን ጠጅ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ፈሰሰው ማንነት ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያል—ዘጸ. 29፥40-41።
   ለ. ሐዋርያው ጳውሎስ በቅዱሳን እምነት መሥዋዕት እና አገልግሎት ላይ የፈሰሰ የመጠጥ ቁርባን ሆነ—ፊልጵ. 2፥17፤ 2 ጢሞ. 4፥6።
   ሐ. የመጠጡ ቁርባን ክርስቶስ ራሱን ብቻ ሳይሆን፣ ለእግዚአብሔር ድሰታ እና እርካታ ደግሞም ለእግዚአብሔር ግንባታ እንፈስ ዘንድ እርሱ እና እኛ አንድ እስክንሆን ድረስ እንደ ሰማያዊው የወይን ጠጅ በራሱ ፈጽሞ የሚሞላንን ክርስቶስንም በምሳሌ ያሳያል—ማቴ. 9፥17፤ ፊልጵ. 2፥17፤ 2 ጢሞ. 4፥6።

*© 2025 Living Stream Ministry*